**መቀበል አቃተን የአባቶችን ትምህርት**

በወያኔ መርሆ በመመራት
ለባእዳን ለመሆን አሽከርነት
ለማዋረድ ኢትዮጵያዊነት
ልባቸውን በፍቅር ነዋይ  ሞልተውት
እያስፋፉ መንደርተኝነት
ጎጠኝነት ከሆዳቸው አዳቅለውት
በእምነት ስም እያስተማሩ ሐሰት

**እንዴት እንቀበል የአባቶችን ትምህርት**

የበግ ለምድ በለበሱ ተኩላዎች
የስደቱን መንጋ ከፋፍለውት
የውግዘትን ትርጉም አዋርደውት
ገዝቻለሁ እያሉ አስፈራርተውት
ትቀሰፋለህ (ትቀሰፊያለሽ) እያሉ በድፍረት
ዲያስፖራውን በታተኑት
ፍቅርን በጥላቻ ቀያይረውት

**መቀበል አቃተን የአባቶችን ትምህርት**

አምልኮቱን ከኑሮ ጋር አዛምዱት
እንደመንጋው ተቀጥራችሁ እዩት
የአሰሪዎችን ግልምጫ ቅመሱት
የመንጋውን ኑሮ ተላመዱት
**እንድታስተምሩን ፍቅርንና እውነት**
**እንድንቀበል ሥነ አምልኮ ትምህርት**

ለኢትዮጵያም ጩሁላት ተሰዉላት
ሰንደቋን ይዛችሁ አውለብልብሏት
ታሪክ መተረኩን በመግታት
ታሪክን እንስራ በአንድነት
እጅ ለእጅ ተያይዘን በእውነት
ኢትዮጵያም ከቁስሏ ትድናለች
በእውነተኛ አባቶችና መንጋዎች
በዝቋላ በዋልድባ በአሰቦት መናኞች።

ከጎላ ምንጭ